# የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የ2012 የፕሮግራም በጀት ጥያቄ

መጋቢት/09/ 2011 ዓ.ም.

<u>አዲስ አበባ</u>

# ማ ው ጫ

1. መግቢያ ........ 1
2. ማጠቃለያ ........ 3
3. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች እና ግቦች ........ 4
ራዕይ፡- ........ 4
ተልዕኮ፡- ........ 4
እሴቶች፡- ........ 4
ዩኒቨርሲቲ አቀፍ ስትራቴጂያዊ ግቦች (Corporate Strategic Objectives)፡- ........ 5
4. ፕሮግራም፣ አላማና ውጤቶች ........ 5
4.1 የሥራ አመራርና የአስተዳደር ፕሮግራም ........ 6
4.2 የመማር-ማስተማር ፕሮግራም ........ 6
4.3 ጥናትና ምርምር ፕሮግራም ........ 6
4.4 የማኅበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራም ........ 7
5. የካፓታል በጀት ፍላጐት ........ 7
5.1 የማጠናከሪያ ነባር (ongoing) ፕሮጀክቶች ........ 7
5.1.1 የውጭ ሀገር መምህራን ደመወዝ፣ የአበልና የትራንስፖርት ወጪ ........ 7
5.1.2 ነባር ግንባታዎች ........ 8
5.2 ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ የነበሩ ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል ........ 8
5.3 በ2012 በጀት ዓመት የሚጀመር ፕሮጀክቶችን ለማስጀመር ........ 8

## 1. መግቢያ

በአገራችን አንጋፋና የመጀመሪያው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሆነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከተቋቋመበት ከ1943 ዓ.ም. ጀምሮ የትምህርት፣ የምርምርና የማህበረሰባዊ አገልግሎት ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርስቲው በ10 ኮሌጆች፣በ2 የቴክኖሎጂ ኢንስትትዩቶች፣ በ3 ትምህርትንና ምርምርን አጣምረው በያዙ ኢንስቲትዩቶች እና በ7 የምርምር ስራ ብቻ በሚያካሄዱ ኢንስቲትዩቶች የተደራጀ ሲሆን፣ በእነዚህምሥር 55 የትምህርት ክፍሎች፣ 12 ማዕከላት፣ 9 ትምህርት ቤቶች እና 2 የማስተማሪያ ሆስፒታሎች ተደራጅተዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በአፍሪካ ቀዳሚ የምርምር ተቋም ለመሆን የሰነቀውን ራዕይ ከማሳካት አንፃር ባደረገው እንቅስቃሴ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞቻችንና የቅበላ አቅማችን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመምጣቱ ከራሱ አልፎ ለሌሎች የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር አቅም ለመፍጠር በሚያስችለው ቁመና ላይ ይገኛል፡፡በአሁኑ ሰአት ዩኒቨርስቲያችን 73 የመጀመሪያ ዲግሪ፣ 205 የ2ኛ ዲግሪ፣ 89 የ3ኛ ዲግሪ፣ 20 ስፔሻሊቲ እና 30 ሰብ ስፔሻሊቲ የቅድመ እና ድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን፣የፕሮግራሞች ስብጥር በመቶኛ ሲሰላም18% የቅድመ-ምረቃ እና 82% የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች ናቸው፡፡

በመማር ማስተማሩ በ2011 የትምህርት ዘመን አዲስ ተማሪዎችን ጨምሮ በአጠቃላይ 47,669 ተማሪዎች በማስተማር ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ 23,993 በመደበኛ መርሃ-ግብር 23,676 ደግሞ መደበኛ ባልሆኑ (የማታ፣የክረምትና ርቀት) መርሃ-ግብሮች ትምህርታቸውንየሚከታተሉ ናቸው፡፡ ይህም የ51% እና 49% እንደቅደምተከተላቸው ምጣኔ ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በፕሮግራም ስታይ በተለይ በ2ኛ እና 3ኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች የቅበላ አቅም አኳያ በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለ2010 የትምህርት ዘመን ከተያዘው የ43,000 እና የ9,000 እቅድ (እንደቅደምተከተላቸው) ዩኒቨርስቲው 4,888 (11.4%) እና 1,424 (15.8%) ተማሪዎችን በመቀበል በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የተቀመጠውን በማሳካት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚሁ የ2011 የትምህርት ዘመን መጨረሻም በቅድመ-ምረቃ 7024 እና ድህረ-ምረቃ 3884 በአጠቃላይ 10908 ተማሪዎችን አስተምሮ ለማስመረቅ ግብ ተጥሏል፡፡

በዩኒቨርስቲያችን ግንባር-ቀደም በሆነው የመማር-ማስተማር ስራ 2790 መምህራን የተሠማሩ ሲሆን፣ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ማጠቃለያ አመት ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከሚያስፈልገው የመምህራን ቁጥር 8.7% ነው፡፡ይህም ስኬት በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የመጀመሪያው ሁለት አመት ጊዜ ውስጥ የተመዘገበ በመሆኑዩኒቨርሲቲያችን በዚህ ረገድ የፈጠረው አቅም ከራሱ አልፎ ለሌሎቹም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እቅድ መሳካት እንደ ግብዓት ሊያግዝ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ የተቋሙን የትምህርት ጥራት ከማስጠበቅ መምህራንን የማብቃትና የትምህርት ደረጃቸውን ማሳደግ አስፈላጊና ምትክ የማይገኝነት ተግባር መሆኑን በመረዳት በተደረገው እንቅስቃሴ በአሁኑ ወቅት ከጠቅላላ መምህራን 17% ዲግሪና ከዚያ በታች ያላቸው ሲሆኑ፣ 41% ሁለተኛ ዲግሪ እንዲሁም 30% 3ኛ ዲግሪ ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፣12% ደግሞ ሀኪሞች ናቸው፡፡

ከአካዳሚያዊ ደረጃ (Academic Rank) አንጻር ሲታይ ደግሞ ከጠቅላላ መምህራን 41% በሌክቸረር (Lecturer) ደረጃ ያሉ ሲሆን፣ 42% ደግሞ ረዳት ፕሮፌሰርናከዚያ በላይ (Assistant, Associate and Full Professors) ናቸው፡፡ የቀሩት 17% ደግሞ ከረዳት መምህር (Assistant Lecturer) እስከ ረዳት ቴክኒሽያን (Technical Assistant) እና ልዩ ልዩ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው፡፡ የመምህራን አቅም የበለጠ ከፍ ለማድረግ አሁንም ከ200 በላይ በተለያዩ ደረጃዎች በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡

በምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ ዩኒቨርስቲያችን በአሁኑ ወቅት ሃገራችን የነደፈቻቸውን የልማት ግቦች መሰረት በማድረግ ቅድሚያ ትኩረት የሚሹ የምርምር ርዕሶችን በመለየት ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለማከናወን ከ600 በላይ ከፍተኛ የዩኒቨርስቲው ተመራማሪዎች የተሳተፉበት 55 የተመረጡ ዙሪያ መለስ የምርምር ፕሮጀክቶች (Thematic Research Projects) እና 26 “adaptive problem solving researches” የምርምር ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርስቲያችን ብቃት ያለው የተማረ የሰው ሀይል በማፍራት፣ችግር ፈቺ ምርምሮችና የእድገትና ልማት አቅም የሚሆኑ ማህበረሰባዊ አገልግሎቶችን በመስጠት የሚያደርጋቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎች ሃገራችን የነደፈችውን የዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ ከማገዝ ባሻገር መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ ለመሰለፍ ለምታደርገው ዘርፈ-ብዙ የልማት ሥራዎች ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ጉልህ አስተዋፅኦ ያላቸው መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ስትራቴጂክ ዕቅድ ይዞ ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ሁሉ እያከናወነ ይገኛል፡፡ ይህንንም ለማሳካት አራት ኘሮግራሞች ማለትም መማር-ማስተማር፣ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ማህበረሰብ አገልግሎት እና አስተዳደርና አመራር አሉት፡፡

ዩኒቨርስቲዉ በአዋጅ የተሰጡትን ተልዕኮዎችና በሁለተኛው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ዕድቅ ለማሳካት በስራ አመራርና አስተዳደር፣ በመማር-ማስተማር፣ በጥናትና ምርምር እንዲሁም ማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራሞች ከመንግስት በሚመደብ በጀት በዕቅድ አመቱ መጨረሻና በቀጣይ የዕቅድ አመታት ራዕዩን ለማሳካት በጀቱን ከዕቅድ ጋር በማስተሳሰር ስኬታማ ዉጤት ለማስመዝገብ ለ2012 በጀት አመት የፕሮግራም በጀት አመት ለጠቅላላ ፕሮግራም ብር 2,219,940,000.00 (ሁለት ቢሊዮን ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ብር ሺህ) በጀት የሚያስፈልገው ሲሆን፣ ጠይቋል፡፡

## 2. ማጠቃለያ

ዩኒቨርስቲዉ በአዋጅ የተሰጡትን ተልዕኮዎችና በሁለተኛው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የታቀደዉን ለማሳካት በስራ አመራርና አስተዳደር፣ በመማር-ማስተማር፣ በጥናትና ምርምር እንዲሁም በማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራሞች ከመንግስት እና ከዉስጥ ገቢ በሚመደብ በጀት በዕቅድ አመቱ መጨረሻና በቀጣይ የዕቅድ አመታት ራዕዩን ለማሳካት በጀቱን ከዕቅድ ጋር በማስተሳሰር የበለጠና የተሻለ ዉጤት ለማስመዝገብ ለ2012 የፕሮግራም በጀት አመት ብር 2,219,940,000.00 (ሁለት ቢሊዮን ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ ብር) የበጀት ጥያቄ አቅርቦል።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባሉት አራት ፕሮግራሞች ማለትም በስራ አመራርና አስተደድር፣ በመማር-ማስተማር፣ ጥናትና ምርምር፣ ማማከርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ለ2011 በጀት አመት ከመንግስት ግምጃ ቤት እና ከዉስጥ ገቢ *የሚያስፈልገውን* አጠቃላይ 1,619,940,000.00 (አንድ ቢሊዬን ስድስት መቶ አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ ብር) ተጠይቋል። ምንም እንኳን በዩኒቨርስቲው ስር የሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች በጀት ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም የተሰጠው ጣራ የዩኒቨርስቲውን ሪዕይና ተልዕኮ ከመተግበር አንፃር ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራትና ውጤቶች ቅድሚያ በመስጠት የበጀት ጣሪያ በገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር የተቀመጠ ጣራ መሠረት በጣም አስፈላጊ ለሆኑ ውጤቶች ብቻ የሚውል እንዲውሉ ጥረት የተደረገ ቢሆንም፣ በተለይም በማኅበረሰብ አገልግሎት እና በካፒታል በጀት ለዩኒቨርሲቲው የተመደበው የበጀት ጣሪያ ላይ ከፍተኛ የበጀት ማነስ ያጋጥመናል የሚል ስጋት አለን።

ዩኒቨርሲቲው በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ስር በሚገኘው የጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል በሃገራችን ብቸኛው የከፍተኛ ህክምና ማዕከል ከመሆኑ አንፃር የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት በተገቢው ጥራትና ደረጃ ለማከናወን በሚያደርገው ጥረትና አገልግሎቱን ከሚፈልገው ተገልጋይ ቁጥር ከፍተኛነት አንፃር በቂ የሆነ በጀት ለማኅበረሰብ አገልግሎት ባለመመደቡ ምክንያት ተደጋጋሚ የበጀት ድጎማ የምንጠይቀበት የበጀት ርዕስ ይሆናል። በ2011-2012 በጀት ዓመትም የያዝነው ብር 240,280,790.00 ከፍላጉቱ ስፋት አንፃር ዝቅተኛ በመሆኑ የበጀት ድጎማ የሚጠየቅበት እንደሚሆን ይታመናል።

ሌላው ከፍተኛ የሆነ የበጀት ጉድለት ያጋጥመናል ብለን የለየነው የካፒታል በጀት ሲሆን፣ ለዚህም ለ2009 በጀት ዓመት ተመድቦልን ከተጠቀምንበት በጀት (ብር 1,137,098,657.87) አንፃር ለ2012 ከተሰጠን የበጀት ጣሪያ (ብር 600,000,000.00) ጋር ሲነፃፀር በ48% ያነሰ ነው። በአበማ 3 በተመለከተው መሠረት አብዛኛዎቹ (16) ዩኒቨርሲቲው ቀጣይ የግንባታዎች ኘሮጀክቱን ከሚያከናውኑት ተቋራጮች ጋር በጊዜ ገደብ በታሰረ ውል ግዴታ የተገባባቸው እና በ2011 በጀት ዓመት ይጠናቀቃሉ ተብሎ የተያዙ እንደመሆናቸው ከሚያስከትሉት የህግ ተጠያቂነትና በወቅቱ ሥራው ባለመካሄዱ ከሚያስከትለው የዋጋ ንረት ተጨማሪ ወጪ፣ የገንዘብና የማቴሪያል ኪሳራ አንፃር ሲታይ የተመደበው በጀት እጅግ አነስተኛ መሆኑ፣ ሌሎች (2) ኘሮጀክቶችም በቅርቡ የሚጠናቀቁና ለታሰበላቸው ዓላማ በማዋል የመማር-ማስተማሩን፣ የምርምሩንና የማኀበረሰብ አገልግሎቱን ሥራ

በሚፈለገው ደረጃና ጥራት ለማከናወን እንዲውሉ ለማድረግ አስፈላጊውን ግብዓት አሟልቶ ወደ ሥራ እንዲገቡ አሁንም ከተመደበው የበጀት ጣሪያ አንፃር ለFurniture, Fixture, Plant, Machineries and Equipment ከፍተኛ የሆነ የበጀት ማነስ እንደሚ

ያጋጥመን በግልጽ ይታያል፡፡ በአጠቃላይ በ2012 በጀት ዓመት እነዚህ ኘሮጀክቶች በተገቢው መንገድ ለማከናወን የሚያስፈልገን ወጪ 1,916,474,140.00 ሲሆን፣ 2012 ከተመደበልን የካፒታል በጀት ጣሪያ (ብር 600,000,000.00) ጋር ሲነፃር ተጨማሪ ገንዘብ ስለሚያስፈልገን በ2011 የካፒታል በጀት ተጨማሪ የበጀት ድጐማ የምንጠይቅበት የበጀት አርዕስት መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በአጠቃላይ ከ2012 ዓ.ም. የኘሮግራም በጀት ጥያቄያችንን ከተሰጠን የበጀት ጣሪያ ጋር በማጣጣም በተቻለ መጠን እንደየኘሮግራሙ ክብደትና ለምንጠብቀው ዩኒቨርሲቲ አቀፍ ውጤት ካላቸው አስተዋጽኦ አንፃር በጀት በመያዝ ያቀረብን ሲሆን፣ የተዘጋጀው ጠቅላላ ፕሮግራም በጀት ከተሰጠው የበጀት ጣሪያ ጋር ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ መሰረት ተነጻጽሯል፡፡

| | መደበኛ በጀት እና የድርጅቱ ገቢ | ካፒታል በጀት | ድምር |
|---|---|---|---|
| የበጀት ጣሪያ | 1,619,940,000.00 | 600,000,000.00 | 2,219,940,000.00 |
| የተጠየቀ | 1,619,940,000.00 | 600,000,000.00 | 2,219,940,000.00 |
| ልዩነት | 0.00 | 0.00 | 0.00 |

## 3. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች እና ግቦች

### ራዕይ፡-

በ2019 ዓ.ም ቀዳሚ ከሆኑ 10 የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ መሆን፡፡

### ተልዕኮ፡-

ብቁ ምሩቃንን በማፍራትና ችግር ፈቺ የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ እንዲሁም ማህበረሰብ ተኮር አገልግሎቶችን በመስጠት የሀገሪቱን የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ልማት ማፋጠን፡፡

### እሴቶች፡-

-የአካዳሚክ ነፃነት
-ልቀት
-ታማኝነት
-እውቀት
-ፍትሃዊነት
-ብዝሃነት
-መረጃና
-ምክንያታዊነት
-ሙስና ተፀያፊነት
-ግልፅነትና
-ተጠያቂነት
-ስራ ፈጠሪነት

## ዩኒቨርሲቲ አቀፍ ስትራቴጂያዊ ግቦች (Corporate Strategic Objectives)፡-

| ዕይታ | ተ.ቁ. | ዩኒቨርስቲ-አቀፍ ግቦች (Corporate objectives) |
|---|---|---|
| ደንበኛ/ባለድርሻ | 1 | ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት የደንበኛ/ባለድርሻ አካላት እርካታን ማሳደግ/መጨመር |
| | 2 | ጥራት ያላቸው የምርምር ውጤቶችን በማቅረብና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ የደንበኛ/ባለድርሻ አካላት እርካታን ማሳደግ/መጨመር |
| | 3 | ጥራት ያለው የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት የደንበኛ/ባለድርሻ አካላት እርካታን ማሳደግ/መጨመር |
| | 4 | የደንበኛ/ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ባለቤትነትን ማሳደግ/መጨመር |
| በጀትና ፋይናንስ | 5 | ውጤታማና ፍትሀዊ የሀብት አጠቃቀምን መተግበር/ማሻሻል/ማሳደግ |
| | 6 | የሀብት ምንጭን ማስፋት/ማሳደግ |
| ውስጥ አሰራር | 7 | የአገልግሎት አሰጣጥ ብቃትና ጥራትን ማሻሻል |
| | 8 | የዩኒቨርስቲውን መልካም ስምና ገጽታ በሀገርና በአለም አቀፍ ደረጃ ማጉላት |
| | 9 | የሀገራዊና ዓለም-ዓቀፋዊ አጋሮችን ትብብር፣ ግንኙነት እና ተሳትፎ ማጠናከር |
| | 10 | የዩኒቨርስቲውን ድርጅታዊ መዋቅር፣ የአሰራር ስርዓትና የአመራር ብቃት ማሻሻል |
| | 11 | የዕውቀት አያያዝ/አጠቃቀም፣ የምርምር ውጤቶች ስርጭት፣ የፈጠራ፣ የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን እና ሽግግርን ማመቻቸት/ማሳለጥ |
| | 12 | የብዝሃነት አያያዝን፣ ጾታዊ እኩልነትን ማሻሻል እና ወቅታዊ/አንገብጋቢ ጉዳዮች ምላሽ መስጠት |
| | 13 | የፕሮግራሞችን አግባብነት ማጥናት/ማሻሻል እና የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞችንና ምርምርን ማቀናጀት |
| መማማርና እድገት | 14 | የሠራተኞችን አቅም ማጎልበት፣ማልማት እና ፍልሰትን መቀነስ |
| | 15 | የመማሪያ፣ የሥራና የመኖሪያ አካባቢ ምቹትን ማሻሻል |
| | 16 | የመሰረተ ልማት ፣ የፋሲሊቲና የኢ.ኮ.ቴ አቅምን ማሳደግ/ማሻሻል |

## 4. ኘሮግራም፣ አላማና ውጤቶች

የፕሮግራም በጀት አሰራር በጀትን ከዉጤት ጋር ለማዛመድ ዉጤትን ለመለካት ተጠያቂነትንና ሀላፊነትን ለማስፈን ፖሊሲንና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ ዕቅድን ከበጀት ጋር ለማስተሳሰር እና የመደበኛና ካፒታል ወጪዎችን ለማቀናጀት የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑ ዩኒቨርስቲዉ ስትራተጂካዊ ዕቅዱን ለመተግበር ለሚያደርጉዉ እንቅስቃሴ የሚያስፈልግ የፕሮግራም በጀት በማዘጋጀት ሲፈቀድም ተግባር ላይ እንደሚያውል ይታወቃል፤

በዚህም መሰረት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመንግስትን የአምስት ዓመት የከፍተኛ ትምህርት የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ የዩኒቨርስቲውን ተልእኮ እና ለአምስት ዓመታት (ከ2008 -2012 በጀት አመት) የተቀመጡትን ስትራቴጂክ ዓላማዎችና ፕሮግራሞችን መሰረት በማድረግ እስካሁን የተደረሰበትን የግብ ስኬት በመገምገም የ2012 በጀት አመት የፕሮግራም በጀት በማዘጋጀት አቅርቧል፡፡

በበጀት ዝግጅቱ ላይ በገ/ኢ/ትብብር ሚኒስቴር የተሰጠውን የፕሮግራም በጀት አዘገጃጀት መመሪያ መሰረት በማድረግ የዩኒቨርስቲው የበላይ ሃላፊዎች ለመነሻ የሚሆን በዕቅዳቸው ላይ የተመሠረተ ፕሮግራም በጀት ሰርተው እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት የተዘጋጀው የፕሮግራም በጀት ዕቅድ የሚከተሉትን አራት አበይት ፕሮግራሞችን ያቀፈ ነው፡፡

## 4.1 የሥራ አመራርና የአስተዳደር ኘሮግራም

የአስተዳደርና አመራር ፕሮግራም ዩኒቨርስቲው የተሰጠውን ዋና ዋና ተልዕኮዎች በብቃትና በውጤታማነት ለመከወን የመልካም አስተዳደር፣የአመራርና አስተዳደር ስርዓት በሁሉም ደረጃዎች በማረጋገጥ መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በተለይም ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ውጤታማነትና ብቃት፣የአቅም ግንባታ ስራዎችና የህግ የበላይነት ልዩ ትኩረት በመስጠት የደንበኞች/ባለድርሻ አካላት እርካታ ከፍ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል፡፡ በዚህም መሰረት የሥራ አመራርና አስተዳደር ፕሮግራም በመማር ማስተማሩ፣በጥናትና ምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራሞች በቀጥታ ሊገለጽ የማይችሉ ውጤቶችንና ይህንንም ለማስገኘት የሚያስችሉ የመደበኛና የካፒታል ፕሮጀክቶች አቅፎ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

***ዓላማ፡-*** በዩኒቨርስቲው ውስጥ የተሻለ የመልካም አስተዳደርና አመራር በማረጋገጥ የደንበኞች/ባለድርሻ አካላት እርካታ ማሳደግ፤

***ውጤት1፡-*** የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች

ለፕሮግራሙ ለ2012 በጀት አመት የተጠየቀ በጀት ብር <u>952,756,740.00</u>

## 4.2 የመማር-ማስተማር ኘሮግራም

ይህ ፕሮግራም በዋነኝነት የገበያውን ፍላጎት የሚሞላና በስራ ፈጠራ የተካኑ ብቁ ዜጋ የማፍራት አላማ ያለው ፕሮግራም ነው፡፡ በተሟላ ተቋማዊ አደረጃጀት ያሉንን የፋይናንስ፣የቁስና የሠው ሀይል አቀናጅቶ በመጠቀም የተሻለ የመማር-ማስተማር አካባቢ መፍጠር ነው፡፡ ይህንን ለማሳካት ተማሪ-ተኮር አቀራረብ፣የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ፣ፍትሀዊነትንና አግባብነት እንዲሁም ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የተማሪ አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ የደንበኛ/ባለድርሻ አካላት እርካታና የዩኒቨርስቲውን ገጽታ ለማሻሻል ነው፡፡

***ዓላማ፡-*** 20000 የገበያውን ፍላጎት (Market-Demand) የሚያሟሉ ብቃት ያላቸውና በስራ ፈጠራ የተካኑ ምሩቃንን ማፍራት

***ውጤት 1፡-*** 20000 የተመረቁ ተማሪዎች

ለፕሮግራሙ ለ2012 በጀት አመት የተጠየቀ በጀት ብር <u>863,979,350.00</u>

## 4.3 ጥናትና ምርምር ኘሮግራም

የጥናትና ምርምር ፕሮግራም በተለዩና በተመረጡ የህብረተሰብ ችግሮች ላይ መሰረታዊ (Basic) እና ተግባር-ተኮር (Applied) ምርምሮችን በማካሄድ እንዲሁም አዳዲስ እወቀቶችን በማመንጨት፣ በማላመድና በማሰራጨት የህብረተሰቡን ችግር መፍታት አላማው ያደረገ ፕሮግራም ነው፡፡ በዚህ ፕሮግራም የዩኒቨርስቲ-ኢንዳስትሪ ትስስር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የጥናትና ምርምር የመረጃ ስርዓት ግንባታ፣ ተደራሽነትና ስርጭት ልዩ ትኩረት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

***ዓላማ፡-*** *መሰረታዊና ችግር ፈቺ ምርምርና ቴክኖሎጂ ማከናወን እና ማሰራጨት፤*

***ውጤት 1፡-*** የተካሄዱ ጥናትና ምርምሮች
***ውጤት 2፡-*** የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች
***ውጤት 3፡-*** የተፈጠሩ የዩኒቨርስቲ-ኢንዳስትሪ ትስስሮች

ለፕሮግራሙ ለ2012 በጀት አመት የተጠየቀ በጀት………………..ብር 74,305,120.00

## 4.4 የማኀበረሰብ አገልግሎት ኘሮግራም

በማህበረሰቡ ቀጣይነት ያለው እድገትና ልማት ለማረጋገጥ ተገቢነት ያላቸውን ማህበረሰባዊ አገልግሎቶች (Initiatives) በመስጠት ብቃት ያለው የማህበረሰብ አገልግሎት ወሳኝ ነው፡፡ በተለይም ፍላጎት-ተኮር (Demand-Driven) የአቅም ግንባታ፣ የማማከር፣ የህክምና አገልግሎቶች በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የሚካተት ይሆናል፡፡

***ዓላማ፡-*** ጥራት ያለው የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት የህብረተሰቡንና የአጋሮቻችንን እርካታ ማሳደግ/መጨመር

***ውጤት 1፡-*** የተሰጡ የስልጠናና የማማከር አገልግሎት
***ውጤት 2፡-*** ለህብረተሰቡ የተሠጡ የሕክምና አገልግሎቶች

ለፕሮግራሙ ለ2012 በጀት አመት የተጠየቀ በጀት………ብር 246,990,790.00

በእነዚህ አራት ዋና ዋና ፕሮግራሞች ሥር አስራ ሁለት ውጤቶች፣ በርካታ ተግባራትና ተግባራቱን ለማስፈፀም የሚረዱ ግብዓቶችን ለማሟላት የሚያስፈልጉ ወጪዎች ተቀምጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት በአራቱም ፕሮግራሞች የተቀመጡትን ውጤቶች ለማስገኘትና ተግባራቶቹንም ለመፈጸም በጠቅላላው ለ2012 በጀት አመት ከመንግስት ግምጃ ቤት 2,138,023,000.00 እና ከ ዉስጥ ገቢ በጀት ብር 81,917,000.00 ተጠይቋል፡፡ለ2012 በጀት አመት ከመንግስት ግምጃ ቤት _እና ከ ዉስጥ ገቢ በጀት ብር 2,219,940,000.00 ተጠይቋል፡፡

# 5. የካፓታል በጀት ፍላጐት

## 5.1 የማጠናከሪያ ነባር (ongoing) ኘሮጀክቶች

በዚህ የፕሮጀክት ርዕስ ስር ከዚህ በፊት በግንባታም ሆነ በሌሎች በፕሮጀክቶች የሚያዙ ተግባራት ተጀምረዉ ያልተጠናቀቁና በሚቀጥለዉ አመትም ለፕሮጀክቶቹ የሚያስፈልግ በጀት በየፕሮጀክት አይነቱ ከሚያስፈልገዉ በጀት ጋር ተዘርዝሮ ቀርቧል::

ነባር (ongoing) ፕሮጀክቶች በሁለት (2) የሚከፈሉ ሲሆን እነዚህም የዉጭ ሀገር መምህራን ደመዎዝ፣የአበልና የትራንስፖርት ወጪ እንዲሁም ነባር ግንባታዎች ናቸው፡፡ የ2012 የበጀት ፍላጎታቸውም ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል፤

### 5.1.1 የውጭ ሀገር መምህራን ደመወዝ፣ የአበልና የትራንስፖርት ወጪ

በአሁኑ ጊዜ እየተሰጠ ያለዉ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ በመስፋፋቱ የድህረ-ምረቃ ተማሪዎችን ለማስተማር ና የዩኒቨርስቲውን አለም-አቀፋዊነት ከፍ ለማድረግ ከዉጭ ሀገር ለሚመጡ 96 የዉጭ ሀገር መምህራን የደመዎዝ፣የአበልና የትራንስፖርት ወጪ በየአመቱ የሚቀጥል በመሆኑ ብር 51,800,000.00 ለ2012 ዓ.ም በጀት አመት ተጠይቋል::

### 5.1.2 ነባር ግንባታዎች

ከዚህ በፊት በግንባታም ሆነ በሌሎች በፕሮጀክቶች የሚያዙ ተግባራት ተጀምረዉ ያልተጠናቀቁና በ2012 በጀት አመትም ለፕሮጀክቶቹ የሚያስፈልግ በጀት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፤

| ተ.ቁ. | የኘሮጀክቱ ስም | የተጠየቀ በጀት (በብር) |
|---|---|---|
| 1. | ለግንባታ | 173,689,990.00 |
| 2. | ለፈርኒቸር (Furniture and Fixture) | 25,510,010.00 |
| 3. | ለትምህርት መሳሪያ (Plant, Machineries and Equipments) | 40,000,000.00 |

በአጠቃላይ የዩኒቨርስቲ ማጠናከሪያ ነባር ፕሮጀክቶች ለ2012 በጀት አመት ብር 291,000,000.00 ተጠይቋል፡፡

## 5.2 ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ የነበሩ ኘሮጀክቶችን ለማስቀጠል

የዩኒቨርስቲው ነባር ፕሮጀክቶች በሦስት ተከፍለዋል፡፡ እነሱም ለመኖሪያ ህንፃዎች ግንባታ (Residential buildings)፣ ለመኖሪያ ያልሆኑ የህንፃዎች ግንባታ (Non-residential building) እና መሠረተ ልማት (Infrastructure) ናቸው፡፡ የ2012 በጀታቸውም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተጠይቋል፤

| ተ.ቁ. | የኘሮጀክቱ ስም | የተጠየቀ በጀት (በብር) |
|---|---|---|
| 1. | በዋናዉ ግቢ የወንዶችና የሴቶች መኝታ ቤት ግንባታ | 10,000,000.00 |
| 2. | በዋናዉ ግቢ ኮምፕሌክስ የሆነ መማሪያ ክፍል እና ስኩል ኦፍ ኮሜርስ ግንባታ | 60,000,000.00 |
| 3. | ጤና ሳይንስ የ5000 ተማሪዎች መኝታ ቤት ግንባታ | 30,000,000.00 |
| 4. | የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት | 50,000,000.00 |
| 5. | የጂኦ ፊዚክስና ስፔስ ሳይንስ (IGSSA) ኢንስቲትዩት ህንጻ ግንባታ | 30,000,000.00 |
| 6. | ባለስምንት ፎቅ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት የቢሮና ላቦራቶሪ ህንጻ ግንባታ | 15,000,000.00 |
| 7. | ለጋዜጠኝነት ትምህርት ቤት ህንፃ ግንባታ | 20,000,000.00 |
| 8. | ለጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተመላላሽ ህክምና መስጫ | 20,000,000.00 |
| 9. | የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ ህንፃ ግንባታ | 18,000,000.00 |
| 10. | ለስፖርት ሳይንስ ጅምናዚየም ግንባታ | 2,000,000.00 |
| 11. | የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች የማደሪያ ህንጻ ግንባታ (Post Graduate Resident Dormitory) | 13,000,000.00 |
| 12. | የመኖሪያ ቤቶች (Residence) ህንጻ ግንባታ | 15,000,000.00 |
| 13. | የፈተናዎች ማዕከል (Testing Center) ህንጻ ግንባታ | 10,000,000.00 |
| 14. | ካሳ ክፍያ ለሰሜን ካምፓስ (AAiT) ፋክሊቲ መሬት ማስፋፊያ | 5,000,000.00 |

በጠቅላላው ከ2006 ጀምሮ ለነበሩ ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል ለ2012 በጀት አመት ብር 303,000,000.00 ተጠይቋል፡፡

## 5.3 በ2012 በጀት ዓመት የሚጀመር ኘሮጀክቶችን ለማስጀመር

የዩኒቨርስቲው ለመኖሪያ ህንፃዎች ግንባታ (Residential buildings)፣ ለመኖሪያ ያልሆኑ የህንፃዎች ግንባታ (Non-residential building) እና መሠረተ ልማት (Infrastructure) ናቸው። የ2012 በጀታቸውም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተጠይቋል፤

| ተ.ቁ. | የኘሮጀክቱ ስም | የተጠየቀ በጀት (በብር) |
|---|---|---|
| 15. | በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመማሪያ ክፍሎች ( Acadamic Complex) ህንጻ ግንባታ | 3,000,000.00 |
| 16. | የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት የድህረ-ምረቃና ምርምር ህንጻ ግንባታ (AAIT Graduate & Research Building) | 2,000,000.00 |
| 17. | የጥርስ ህክምና ት/ቤት ህንጻ ግንባታ ስራ ማከናወን (ለመማሪያ ክፍል፤ለህክምና እነ ቢሮዎች) | 1,000,000.00 |
| 18. | የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የእንሰሳት ህክምና ግብርና ኮሌጅ የቢሮና የመማሪያ ክፍል የያዘ ህንጻ | 1,000,000.00 |
| 19. | የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የእንሰሳት ህክምና ግብርና ኮሌጅ የሰራተኞች መኖሪያ ህንጻ | 1,000,000.00 |
| 20. | የድባብ መናፈሻ የማስፋፊያ ስራ | 2,000,000.00 |
| 21. | የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ የተማሪዎች ካፊቴሪያ ማስፋፊያ (Cafeteria renovation at Natural science campus) | 1,000,000.00 |

በጠቅላላው ከ2012 ጀምሮ ፕሮጄክቶችን ለማስጀመር ለ2012 በጀት አመት ብር 11,000,000.00 ተጠይቋል።